# ነጋ ደግሞ !

አሥራደው (ከፈረንሳይ)



ላስታምም የሆዴን ጩርር ..... ርታ፤

ላዳምጥ የወስፋቶቼን ጩኸት ጫጫታ፤

የማያቋርጥ የረሃብ ሳል ልስል፤

እሹሩሩ  እያልኩ ረሃብን ላባብል፤

ልደማ ልቆስል ልገዘገዝ በችጋር፤

በቁም  ሞቼ - ላልኖር ስኖር፤

በብርሃኗ ላላጌጥ - ጮራዋ ለኔ ላይፈነጥቅ፤

ነጋ ደሞ ! ...... ሌላ ቀን - ፀሐይ ወ'ታ ልትጠልቅ ::

ነጋ ደግሞ !

ጅራፍ ሆኖ የሰው ዓይን ሊገርፈኝ፤

ማጣት መስታወት ሆኖ  የሰው እጅ ሊያሳየኝ፤

ሊያደርገኝ ቀላዋጭ የበይ ተመልካች ፤

የገዛ አገሩ ሃብት ተመጽዋች፤

ደሞ ነጋ !..... የማልበላውን ምግብ ላሸት፤

ሲጎርሱ ሲጎራረሱ ልመለከት፤

ባልበላሁት ምግብ ምች ሊመታኝ፤

እነሱ በበሉ እኔን ሊያገሳኝ ::

ነጋ ደግሞ !

በነ እንቶኔ ሙዚቃ፤

ጆሮዬ ሊደቃ፤

የጆሮዬ ብራና ሊጠለዝ፤

እንደከበሮ ሊነረት ሊጦዝ፤

በነሱ ጉሮሮ ውስኪ ሲንቆረቆር፤

እነሱ በጠጡት እኔ ልሰክር ::

ደሞ ነጋ ! ... ተሽሞንሙነው ለብሰው ሊወጡ፤

ሊያምርባቸው በኔ ስቃይ - በኔ ማጣት ሊያጌጡ ::

ነጋ ደግሞ !

የግፍ ጽዋ ልጨልጥ፤

የበደል እንቆቆ ልውጥ፤

በረሃብ ጅራፍ ልገረፍ፤

በብርድ ቆፈን ልንዘፈዘፍ፤

ከአገሬ - ከትውልድ መንደሬ ልነቀል፤

ትውልድ ላልተካ ዘር ሆኜ ላልበቅል ::

ገና ከጥዋቱ በጨቅላነት ልቀጭ፤

ሊመነገል ስሬ ሊቀጭጭ፤

ነጋ ደሞ ! ..... ሌላ ቀን - ፀሐይ ወ'ታ ልትጠልቅ፤

በብርሃኗ ላላጌጥ - ጮራዋ ለ'ኔ ላይፈነጥቅ ::

ነጋ ደግሞ !....... ሌላ ቀን...... !

በፍትህ እጦት፤ በኑሮ ውድነትና፤ ከሚኖሩበት ቦታ በመፈናቀል፤ ለሚሰቃዩ ወገኖቼ ማስታወሻ ትሆን ዘንድ የተቋጨች::

መጋቢት 12 ቀን 2006 ዓ.ም. (March 21/ 2014)